በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት

ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የሴክሬታሪያቱን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ
የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን የግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያትን የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 16 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 4 ገጽ አባሪ በድምሩ 20 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 21 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል።

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የሴክሬታሪያቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው።

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ኦዲታችን የሚያካትተው፡ -

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ሥራ አመራር በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ ታኅሳስ 5 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAGF-02.5/11/2 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት የግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያቱ ታኅሳስ 12 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 15/347/2010 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የወጪ ሂሳብ

1.1 ከቤት አበልና ከተለያዩ ጥቅማጥቅሞች ላይ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር፤

1.1.1 ግኝት

በገቢ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ….ወዘተ ከወር ደመወዝ ጋር እተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አሳውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ለሴክሬታሪያቱ በመስከረም 3 ቀን 2009 ዓ.ም ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተፈቅዶ የነበረው የቤት አበልና የልጆች የትምህርት ቤት በየደረጃው ለሚገኙ የምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ የሥራ ኃላፊዎችና ተመራማሪዎች ተፈቅዷል፡፡ ሆኖም ከህዳር 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2009 ዓ.ም ድረስ ከተፈጸመው ክፍያ ላይ ብር **171,457.50** የሥራ ግብር ተቀናሽ ያለመደረጉ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

1.1.2 ሥጋት

☞ መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ያሳጣዋል፡፡

☞ መንግሥት ያወጣውን አዋጅ ደንብና መመሪያ ተከትሎ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ክፍያው ከተፈቀደበት ቀን ጀምሮ ያለው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከቤት አበል እና ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ያልተቀነሰ የስራ ግብርን በተመለከተ በኦዲት ግኝቱ የተጠቀሰው ሃሣብ ትክክል ቢሆንም የተፈቀደው የጥቅማ ጥቅሞች ፓኬጅ ከሌሎች መሰል ተቋማት ጋር ሲፈቀድ ከግብር ነጻ ናቸው የሚል በመሆኑ ሳይቆረጥ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ከገንዘብ እና ኢኪኖሚ ትብብር ሚኑስቴር መሰከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር እንመ1/1/3 በተጻፈ ደበዳቤ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ተቋማችን ይህንን አሰራር በመቀየር መቆረጥ የተጀመረ መሆኑን እያረጋገጥን ቀደም ብሎ ሳይቆረጥ የተከፈለውን አበል ለማስመለስ በአገር ደረጃ ተመራማሪዎችን በምርምር ስርዓቱ ከማቆየት አንጻር ወሳኝ በመሆኑ ሌሎች መሰል ተቋማት ጉዳዩን ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አሳውቀው ምላሽ በመጠባበቅ ላይ በመሆናቸው ያልተመለሰ መሆኑን እንገልጻለን ሂደቱንም በመከታተል ተቋማችን የሚተገበር መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

1.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ያልተቀነሰው የሥራ ግብር ብር 171,457.50 ተቀናሽ ተደርጎ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም በወጣው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲቀነስ እናሳስባለን፡፡

1.2 ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ፤

1.2.1 ግኝት

ለሴክሬታሪያቱ ሰራተኞች የሚከፈለው የውሎ አበል የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሰኔ 2004 ዓ.ም ባወጣው የመንግሥት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈፃም መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር (2) እና (3) መሰረት:-

- ከሙሉ አንድ ቀን የዉሎ አበል ተመን ዉስጥ 10% ለቁርስ 25% ለምሳ 25% ለእራት እና 40% ለአልጋ በመመደብ፤
- መሥሪያ ቤቱ የምግብ ወይም የመኝታ አገልገሎት የሰጠ እንደሆነ የተሰጠዉ አገልገሎት ሂሳብ ከላይ በተመለከተዉ ተመን መሰረት ከዉሎ አበል ተቀናሽ እንደሚሆን፤

ተመልክቷል። ከዚህም በተጨማሪ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ለሴክሬታሪያቱ መስከረም 3 ቀን 2009 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በፈቀደው የውሎ አበል መጠንን መሰረት በማድረግ ከላይ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ባስቀመጠው ታሪፍ መሰረት የውሎ አበል ክፍያዎች የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ:-

1. የምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ በተለያዩ ቦታዎች ባካሄደው ወርክሾፕ ላይ ለተሳታፊዎች ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት በተፈቀደው የውሎ አበል መጠን መሰረት ብር 2,426,562.36 ሙሉ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣ ከመመሪያው ውጪ ተሳታፊዎች በየመንገዱ ምግብና የመሳሰሉትን ተጠቅመው ለፈጸሙት ክፍያ ብር 316,716.85 በአቀረቡት ደረሰኝ መሰረት ሂሳቡ እንዲወራረድላቸው የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

2. ለሥልጠና ተሳታፊዎች ለውሎ አበል ከተፈጸመው ክፍያ ብር 2,426,562.36 ውስጥ ብር 2,101,382..36 የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመላቸው ሰራተኞች ወይም ተሳታፊዎች ማንነት፣ የደመወዛቸው መጠን የሚገልጽ እንዲሁም ከመጡበት መሥሪያ ቤት የውሎ አበል ክፍያ አለመፈጸሙን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ

ባለመጻፉ (ባለመቅረቡ) ምክንያት የተፈጸመውን የውሎ አበል ክፍያ አግባብነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።

(ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

1.2.2 ሥጋት

- የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።
- በውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥራው ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

1.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በስልጠና ተሳታፊ ለመሆኑ ከተለያዩ ክልሎችና መሥሪያ ቤቶች ተወክለው የሚመጡ ተሳታፊዎች ከመጡበት መሥሪያ ቤት ደብዳቤ ይዘው ሊቀርቡ ይገባል። እንዲሁም የውሎ አበል ተከፍሎ እያለ አለአግባብ ለምግብ ክፍያ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል። ለወደፊቱ በውሎ አበል አከፋፈል ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

1.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያን በተመለከተ ሰክሬታሪያቱ የተቋቋመበትን አገራዊ የግብርና ምርምርን የማስተባበር ኃላፊነት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚደረገው የተለያዩ ወሳኝ ሰነዶችን ዝግጅት እና የውይይት መድረክ ከተሳታፊዎችን የሚጠበቀውን አስተዋጽኦ በአንድ አካባቢ አሰባስቦ በአጭር ጊዜ ለማስፈጸም የውሎ አበል ለማይከፈላቸው እና በውይይት መድረኮቹ አካባቢ ለሚገኙ ተሳታፊዎች የመስተንግዶ ወጪ የመክፈል ሥርዓት የነበረ መሆኑን እየገለጽን ከሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ምንም ዓይነት የሆቴል መስተንግዶ ክፍያ ያልተፈጸመ መሆኑን እና የነበሩት ክፍተቶች በመታረም ሂደት ላይ መሆናቸውን እናረጋግጣለን።

1.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት

1. የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ለሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከተፈቀደው የቀን የውሎ አበል መጠን በላይ የተሻለ የውሎ አበል ክፍያ መጠን ለሴክሬታሪያቱ ፈቅዷል፡፡ ሆኖም ሴክሬታሪያቱ ለውይይቱ ተሳታፊዎች የሙሉ ቀን አበል ክፍያ ፈጽሞ እያለ በድጋሚ ለምግብ በደረሰኝ ክፍያ መፈጸሙ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡
2. ሥልጠና (ወርክ ሾፕ) ሲዘጋጅ ተሳታፊዎቹን ማንነትን፣ የደመወዛቸውን መጠን የሚገልጽ እንዲሁም ከመጡበት መሥሪያ ቤት የውሎ አበል ክፍያ አለመፈጸሙን ለማረጋገጥ የሚያስችል ደብዳቤ ከመጡበት መሥሪያ ቤት (ክልል) ይዘው እንዲቀርቡ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.3. በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በፕሮፎርማ የተፈጸመ ግዥ፤

1.3.1. ግኝት

ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣው መመሪያ መሰረት ከብር 200,000.00 በላይ የሚፈጸሙ ግዥዎች በግልጽ ጨረታ የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያቱ በጠቅላላው በብር 1,120,982.27 የአልሙኒየም ፓርትሽን ሥራ ያሰራ እና የተለያዩ ቋሚ አቃዎች ግዥ የፈጸመ ሲሆን ግዥውን ግልጽ ጨረታ ሳያወጣ በዋጋ ማወዳደሪያ ያከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

1.3.2. ሥጋት

☞ በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

☞ የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፈና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል ያደርጋል።

☞ ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

☞ ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ይችላል።

1.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ የምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

1.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ተቋሙ አዲስ እንደመሆኑ የነበረበት የቢሮ እጥረት ጫናና ቢሮውን ተከራይቶ የመንግሥት ገንዘብ በኪራይ ያለምንም ጥቅም ማዋሉ አስጨናቂ ስለነበር በግልጽ ጨረታ መግዛት ሲገባው በኘሮፎርማ የተፈጸመ ግዥን በተመለከተ ሰክሬታሪያቱ የሚገለገልበት ህንጻ በኪራይ የተገኘ በመሆኑ ቢሮዎቹን በአስቸኳይ አደራጅቶ ወደ ተግባር ለመግባት በተደረገው ጥረት የሴክሬታሪያቱ ሥራ አመራር ተሰብስቦ የህንጻውን የተወሰነ ክፍያ በፓርትሽን ሲሰራ የነበረው ድርጅት ከሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶች አነስተኛ ዋጋ በማቅረቡ ሲሆን ለወደፊቱ ሴክሬታሪያቱ ህግና ደንብን ተከትሎ መሰል የአገልግሎት ግዥዎችን የሚፈጽም መሆኑን እንገልጻለን።

1.3.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ግዥው የተፈጸመው በዋጋ ማወዳደሪያ ከተወዳደሩት አነስተኛ ዋጋ ካቀረበው አቅራቢ ቢሆንም በአዋጁና በመመሪያው መሠረት ግዥው በግልጽ ጨረታ መፈጸም ነበረበት። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በአብዛኛው ግዥዎችን በእቅድ ካለመምራት የሚከሰት ነው። ሴክሬታሪያቱ የጊዜ ውስኑነት ካጋጠመው በግዥ መመሪያው አንቀጽ 31 መሰረት መደበኛ

ያልሆኑ የግዢ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩትን የግዢ አፈጻጸም ሥርዓቶች ሊጠብቅ ካልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዢ ለመፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት በቅድሚያ ለግዥ ኤጀንሲ አቅርቦ ማስፈቀድ ነበረበት። ስለሆነም ለወደፊቱ ሴክሬታሪያቱ የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን መፈጸም እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

1.4. <u>በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ፤</u>

1.4.1. <u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ከተለያዩ ግዥዎችና ክፍያዎች በድምሩ ብር 355,712.68 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

1.4.2. <u>ሥጋት</u>

- የሂሳብ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- በሂሳብ መግለጫው ተጠቃሚዎች የተሳሳተ መረጃ ሊሰጥ ይችላል።

1.4.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በስህተት ለተመዘገቡት ሂሳቦች ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራላቸው ይገባል። በተጨማሪም ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

1.4.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በትክክለኛ የሂሣብ መደብ ያልተመዘገበውን ግኝት የምንቀበለው እና ትክክል ሲሆን ችግሩ የተፈጠረው በወቅቱ ሴክሬታሪያቱ የራሱ የሆነ የሂሣብ እና የበጀት ሰራተኛ የሌለው ከመሆኑ በተጨማሪ ለዓመት

ከተፈቀደለት በጀት ያልተጠቀመባቸውን የሂሣብ መደቦች በወቅቱ አስፈላጊው የበጀት ዝውውር ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሳይጠየቅ ገንዘቡ ወደ ባንክ የገባ በመሆኑ ሁኔታውን በውስጥ ማስታወሻ ለዋና አስተባባሪው አስታውቀን የሂሣብ ማስተካከያ ሥራ የተሰራ ነበር፡፡ ሆኖም ይህን አይነት አሰራር ህጋዊ ለማድረግ በአሁኑ ወቀት በቂ የሆነ የሰው ኃይል በመሟላቱ ለወደፊት የማይደገም መሆኑን እንገልጻለን፡፡

1.4.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ለሂሳቡ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም ወጪዎች በተገቢው የሂሳብ መደብ ይመዘገቡ ዘንድ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

1.5. ያለበጀት አመቱ የተመዘገበ ሂሳብ፤

1.5.1. ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት በ2009 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሰረት መሆኑን እና የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ከሐምሌ 17 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 21 ቀን 2009 በዱብቲ ለተካሄደው ሥልጠና ሰኔ 30 ቀን 2009 በወጪ ቫውቸር ቁጥር 71414 የተፈጸመው ክፍያ ብር 174,491.85 በ2010 በጀት ዓመት መመዝገብ ሲገባው በ2009 ተከፍሎና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

1.5.2. ሥጋት

የበጀት ዓመቱ የሒሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

1.5.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በኦዲት ግኝቱ የታየው ያለበጀት ዓመቱ የወጣው ወጪ ምክንያት ስልጠናው በሰኔ ወር 2009 በሁለት ዙር ታቅዶ ገንዘቡ ወጪ ሆኖ የነበረና በተለያዩ ምክንያቶች የሁለተኛው ዙር ስልጠና ወደ ሀምሌ ወር 2009 በመተላለፉ የተፈጠረ መሆኑን እየገለጽን ለወደፊቱ አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ ወጪዎች በተያዘላቸው የበጀት ዓመት እንዲከናወኑ የሚደረግ መሆኑን እንገልጻለን።

1.5.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ያለበጀት ዓመት የተመዘገበ ሂሣብን በተመለከተ ችግሩ የተከሰተው በሰኔ ወር ይካሄዳል ተብሎ ሳይካሄድ በቀረ ሥልጠና ሲሆን በጀቱ የ2009 ዓ.ም በመሆኑ እና የወጪ ምዝገባ ማዘዣ ስላልተዘጋ እና ወጪውም በ2009 በጀት ዓመት ተመዝግቦ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ከተደረገ በኋላ የታየ ስህተት መሆኑን አምነን ወደፊት የሚመዘገቡ ወጪዎች በየበጀት አመቱ በአግባቡ የምንመዘግብ መሆኑን እናሳውቃለን።

2. ንብረት

2.1. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ ክፍተቶች፤

2.1.1. ግኝት

የግብርና ምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦

☞ አላቂ እቃዎች በስቶክ ካርድ የማይመዘገቡ መሆኑ፤

- ☞ የንብረት መመዝገብ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ማዘጋጀትና የንብረት መጠበቅ ሥራ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፤
- ☞ በግብርና ምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ ያሉ ቋሚ ንብረቶች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን ለእያንዳንዱ ንብረት የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጀው ቅጽ መሠረት ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት በመጠቀም ያልተመዘገበቡ መሆኑ፤
- ☞ በየቢሮው የሚገኙት ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- ☞ ለቋሚ ንብረት ተጠቃሚ ሠራተኞች የንብረት ምዝገባ ካርድ User Card) ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

2.1.2. <u>ሥጋት</u>

- ☞ መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- ☞ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሰረት የንብረት ያዥና የንብረት መዝጋቢ ሰራተኛ ካልተለያየ ለጥፋትና ለጉድለት መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

2.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አጠቃቀም፣ አጠባበቅና አያያዝ መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈጸም ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.4. የሥራ አመራር ምላሽ

የተጠቀሰው ግኝት ትክክል መሆኑን እየገለጽን ገና በመደራጀት እና በመቋቋም ያለ አዲስ ተቋም በመሆኑ እና የሰራተኛ ቅጥሩም በወቅቱ ያልተከናወነ ስለነበር የተፈጠሩ ክፍተቶች መሆኑን እየገለጽን በአሁኑ ወቅትም አስፈላጊው ሰራተኛ ተቀጥሮ የንብረት ምዝገባና ቁጥጥር በአግባቡ እየተከናወነ መሆኑን እንገልጻለን።

3. በጀት

3.1. ሥራ ላይ ያልዋለና ከተደለደለው በላይ የወጣ የወጪ በጀት፤

3.1.1. ግኝት

ለምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ በ2009 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ውስጥ ከ10% በላይ ብር 2,879,176.86 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፣ ብር 1,433,280.33 ደግሞ ለየሂሳብ ኮዱ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑ ታውቋል።
(ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

3.1.2. ሥጋት

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የመሥሪያ ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።

3.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በኀላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በጀቱ ሥራ ላይ ያልዋለው ሴክሬታሪቱ ጀማሪ ተቋም ከመሆኑ አንጻር በተለይ በሂሣብ መደብ 6243 (ለህንጻ እድሳት)፣ 6254 (ለኢንሹራንስ) እና 6259 (ለውሃ እና ፖስታ አገልግሎት) የተመደበለትን በጀት ምንም ያልተጠቀመ እንዲሁም የደመወዝና ጥቅማጥቅም የበጀት መደቦች የሰክሬታሪያቱ የሰው ኃይል ባለመሟላቱ የታየ ክፍተት ሲሆን፤ ከበጀት በላይ የተጠቀመውን በተመለከተ ለተቋሙ አስፈላጊ የሆኑ የቋሚ እቃ መገልገያዎችን ማለትም የጠረጴዛ፣ የወንበሮች፣ የኮምፒውተር እና የላፕቶፕ ግዥ በመፈጸሙ ከበጀት በላይ የተካሄደ መሆኑን አምነን ወደፊት እንደዚህ አይነት ስህተት እንደማይከሰት እናሳውቃለን።

3.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

1. የምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ የበጀት እጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ህጉን ተከትሎ ዝውውር ሊጠይቅ ይገባል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ክፍያ መፈጸም ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ይችላል።
2. የምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርበታል።

4. ልዩ ልዩ

4.1. ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬቱ የሰራተኞች ቅጥር ያልተከናወነ ስለመሆኑ፤

4.1.1. ግኝት

በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በፋይናንስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር

47/2009 መሰረት እንዲሁም በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዉስጥ ኦዲት ክፍል በየሩብ አመቱ የመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራርና ሠራተኞች ኃላፊነታቸዉን በብቃት መወጣት እንዲችሉ በተዘረጋዉ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በሥራ ላይ ባሉት ህጎችና የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት ስራዎች መከናወናቸዉን ኦዲት እያደረገ በመመሪያዉ ላይ በተቀመጡት ግዜ ዉስጥ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ ለዳይሬክቶሬቱ በመዋቅር ኃይል አራት የኦዲት ባለሙያ የተፈቀደ ቢሆንም ምንም አይነት ቅጥር ያልተፈጸመ መሆኑ እና በዚህም ምክንያት የበጀት ዓመቱ ሂሳብ ኦዲት ያልተደረገና የፈሰስ ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.1.2. ሥጋት

- ✓ በቀላሉ ሊቀረፉ የሚችሉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች ሳይታዩ ሊታለፉ ይችላሉ፡፡
- ✓ በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በአዲሱ የፋይናንስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 47/2009 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የውስጥ ኦዲት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲሆን የተደረገ በመሆኑ፣ ለውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመዋቅሩ በተፈቀደው መሰረት ተገቢው የሰው ኃይል እንዲሟላለት ሴክሬታሪያቱ የገ/ኢ/ት/ሚ/ር በመጠየቅ የተሟላና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል በመመደብ (በመቅጠር) የሥጋት አካባቢዎችን ለይቶ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የኦዲቱን ሥራ በማከናወን እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻም በፈሰስ ሂሳብ ሥራ ላይ በመሳተፍ ሪፖርት እንዲያቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በግኝቱ እንደተጠቀሰው ሴክሬታርያቱ አዲስ የተቋቋመ በመሆኑ የውስጥ ኦዲተር የሌለው ቢሆንም ክፍተቱን በቅጥር ለመሙላት ማስታወቂያ ወጥቶ በአሁኑ ወቅት የኦዲት ዳይሬክተር ለመቅጠር ፈተና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በኩል ተሰጥቶ ያለፉት ተወዳዳሪ የቅጥር ፎርማሊቲ በማሟላት ላይ የሚገኙ መሆኑን እንገልጻለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በግብርና ምርምር ምክር ቤቱ እና ሴክሬታሪያቱ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

<u>ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራ ግብር ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	ገንዘቡ የተከፈለው	የወር ደመወዝ	የኃላፊነት አበል	በወር የተከፈለው የልጆች የት/ቤት፣ የቤት አበል መጠን	ጠቅላላ ተከፋይ	በወር የተቀነሰ የሥራ ግብር	በወር መቀነስ የነበረበት ሥራ ግብር	በወር ያልተቀነሰ ሥራ ግብር	ክፍያው የተፈጸመበት ወሮች ብዛት	ጠቅላላ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር
1	ዶ/ር መኩሪያ ታደሰ	14,116.00	3,000.00	11,000.00	28,116.00	4,490.60	8,340.60	3,850.00	2	7,700.00
	ዶ/ር መኩሪያ ታደሰ	15,067.00	3,000.00	11,000.00	29,067.00	4,823.00	8,673.45	3,850.45	6	23,102.70
2	ዶ/ር ጌትነት አልማው	12,069.00	2,000.00	9,000.00	23,069.00	3,424.25	6,574.15	3,149.90	1	3,149.90
	ዶ/ር ጌትነት አልማው	14,116.00	2,000.00	11,000.00	27,116.00	4,140.00	7,990.60	3,850.60	7	26,954.20
3	ዶ/ር መንግሥቱ አለማየሁ	12,069.00	2,000.00	9,000.00	23,069.00	3,424.15	6,574.15	3,150.00	1	3,150.00
	ዶ/ር መንግስቱ አለማየሁ	12,069.00	2,000.00	11,000.00	25,069.00	3,424.15	7,274.15	3,850.00	7	26,950.00
4	ዶ/ር መላኩ አለሙ	8,651.00	2,000.00	7,000.00	17,651.00	2,240.30	4,677.85	2,437.55	1	2,437.55
	ዶ/ር መላኩ አለሙ	8,651.00	2,000.00	10,000.00	20,651.00	2,240.00	5,727.85	3,487.85	1	3,487.85
	ዶ/ር መላኩ አለሙ	10,234.00	2,000.00	10,000.00	22,234.00	2,781.90	6,281.90	3,500.00	6	21,000.00
5	አቶ ጌታቸው አለሙ	12,069.00	2,000.00	8,000.00	22,069.00	3,424.25	6,224.15	2,799.90	1	2,799.90
	አቶ ጌታቸው አለሙ	12,069.00	2,000.00	10,000.00	24,069.00	3,424.15	6,924.15	3,500.00	7	24,500.00
6	አቶ ሚኒሊክ ጸጋ	8,651.00	2,000.00	5,000.00	15,651.00	2,240.30	3,977.85	1,737.55	1	1,737.55
	አቶ ሚኒሊክ ጸጋ	8,651.00	2,000.00	10,000.00	20,651.00	2,240.00	5,727.85	3,487.85	1	3,487.85
	አቶ ሚኒሊክ ጸጋ	10,234.00	2,000.00	10,000.00	22,234.00	2,781.90	6,281.90	3,500.00	6	21,000.00
	ድምር				320,716.00	45,098.95	91,250.60	91,250.60		171,457.50

አባሪ. 2

<u>የውሎ አበል ተከፍሎ እያለ አለአግባብ የምግብ በደረሰኝ የተወራረደ ሂሳብ ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	ቀን	የቫውቸር ቁጥር	የወጭው ምክንያት	ለውሎ አበል የተከፈለ	ለምግብ በደረሰኝ የተወራረደ
1	30/10/09	717626	ከ25/6/2009 እስከ 03/7/2009 በአዳማ ለተካሄደው አውደ ጥናት	**88,972.00**	**10,534.74**
2	30/10/09	717644	ከ8/08/2009 እስከ 11/08/2009 ለተካሄደው የምክክር መድረክ ወጪ የሆነ	**100,233.00**	**3,401.71**
3	07/07/09	717609	ከ28/5/2009 እስከ 30/05/2009 ተንዳሆ ስኳር ፕሮጀክት ለተካሄደው ወርክ ሾፕ	**84,644.00**	**12,450.00**
4	30/10/09	717642	በ2009 መልካሳ አግሪ ካልቸር ስልጠና የተሰጠበት	**50,5570.00**	**2,092.31**
5	01/07/09	717608	ከ10/102009 እስከ 30/10/2009 በሁመራ ለተካሄደው ወርክ ሾፕ ወጪ የሆነ	**145,133.00**	**17,749.36**
6	30/10/09	717643	ከ12/09/2009 እስከ 14/09/2009 በሀዋሳ ለተካሄደው ስልጠና ወጪ የሆነ	**235,356.26**	**25,587.00**
7	30/10/09	717645- 46	ከ04/09/2009 እስከ 27/09/2009 ድረስ ለተካሄደው ወርክሾፕ	**278,613.00**	**13,080.86**
8	30/10/09	717647- 48	ከ02/09/2009 እስከ 09/09/2009 በሁመራ ከተማና በመቀሌ ለተካሄደው ወርክሾፕ	**584,752.00**	**118,525.08**
9	30/10/09	717646 - 47	አርባ ምንጭ ከ21/04/2009 እስከ 22/04/2009 ድረስ ለተካሄደው ወርክሾፕ	**136,426.00**	**22,973.65**
10	30/10/09	71414 063	በዱብቲ ከታህሳስ 20/04/2009 እስከ 21/04/2009 ድረስ ለተካሄደው ወርክሾፕ	**172,083.60**	**12,027.14**
11	30/10/09	71408 57	በሁመራ ከ20/10/2009 እስከ 30/10/2009 ድረስ ለተካሄደው ወርክሾፕ	**94,779.50**	**78,295**
ድምር				**2,426,562.36**	**316,716.85**

አባሪ .3

__በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በፕሮፎርማ የተፈጸመ ግዥ፤__

ቀን	የቫውቸር ቁጥር	ክፍያው የተፈጸመው ድርጅት	የሂሳብ መደብ	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
23/09/09	**717621-22**	ምንአየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	**6313**	የተለያዩ ቋሚ እቃዎች ግዢ	238,900.00
28/10/09	717637-38	ሳቤህ አልሙኒየምና ብረታ ብረት ስራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	**6314**	አልሙኒየም ፓርቲሽን የተሰራበት	882,082.27
ድምር					**1,120,982.27**

አባሪ. 4

__**በትክክለኛው (በተገቢው) የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ሂሳብ ዝርዝር፤**__

ወጪ የተያዘበት ቀን	የወጪ ደረሰኝ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የወጪው የሂሳብ መደብ		የገንዘብ ልክ
			የተመዘገበው	መመዝገብ የነበረበት	
30/10/2009	711414	ለስልጠና ወጪ የሆነ	6231	6271	245,513.00
30/10/2009	711413	የመስታወት እስቲከር የተገዛበት	6233	6219	110,199.68
ድምር					**355,712.68**

አባሪ. 5

ያልተሰራበት በጀትና ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ዝርዝር፤

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት		
			ያልተሰራበት	ከበጀት በላይ የወጣ	በፐርሰንት (%)
6111	2,463,200.00	571,820.00	1,891,380.00		77
6114	56,700.00	23,200.00	33,500.00		59
6131	281,760.00	62,900.20	218,859.80		78
6211	12,000.00	4,882.44	7,117.56		59
6213	200,000.00	177,114.85	22,885.15		11
6217	300,000.00	250,149.11	49,850.89		17
6218	30,100.00	22,120.05	7,979.95		27
6233	500,000.00	307,095.16	192,904.84		39
6241	200,000.00	72,999.26	127,000.74		64
6243	22,000.00		22,000.00		100
6253	40,000.00	11,182.30	28,817.70		72
6254	116,000.00		116,000.00		100
6257	18,000.00	4,995.00	13,005.00		72
6258	180,000.00	40,324.77	139,675.23		78
6259	8,200.00		8,200.00		100
6313	1,750,000.00	3,183,280.33		1,433,280.33	82
ድምር	**6,177,960.00**	**4,732,063.47**	**2,879,176.86**	**1,433,280.33**	

<u>በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር</u>

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ___________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ___________________________

የተዘጋጀበት ቀን:- __________________

ተራ ቁጥር	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች	እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ7 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።